ምረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ምወዐድ)
Moresh Wegenie Amara Organization (MWAO)

Website: www.moreshwegenie.org    E-mail: infoandpr@moreshwegenie.org

ትግላችን ትውልድ ተሻጋሪ ነው። የዐማራው መደራጀት የኅልውናው እና የማንነቱ መሠረት ነው።
Our struggle is trans-generation. Amara's organization is the basis of its existence and identity.

*ምረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት*    *ረቡዕ መጋቢት ፱  ቀን ፪ሺህ፲፪ዓ.ም.*    *ቅጽ ፯ቁጥር ፲፫*

# ሀገሪቱ ላይ ላንዣበበው የወረረሽኝ በሽታ አስጊ አደጋ ተገቢና እውነተኛ እርምጃ በመውሰድ ህዝባችንን እንታደገው!

በአለም ላይ ከፍተኛ የገንዘብ፣ የቴክኖሎጂ፣ የህክምና ተቋማት ባለቤት የሆኑ ሀገሮች የCOVID19 ወረርሽኝን ለመቋቋም ከሚያደርጉት ሀገራዊ ጥንቃቄና አፋጣኝ የተግባር እንቅስቃሴ አንፃር፣ በኢትዮጵያ ተገቢው የህዝቡን ደህንነት የመጠበቅ ጥረት እየተደረገ አለመሆኑ የሚታይ ሀቅ ነው። ይህ የወረርሽኝ አደጋ በብዙ ሺዎች ብቻ ሳይሆን በሚሊዮኖች የሚቆጠር ወገናችንን በሞት ሊቀጥፍ የሚችል መሆኑን በማጤን የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና የሲቪክ ድርጅቶች በሙሉ በየፊናቸው የህዝቡን አኗኗርና መስተጋብር ያገናዘበ የተግባር እንቅስቃሴ የማድረግ ለነገ የማይባል ሀላፊነት አለባችሁ። ይህን ሳታደርጉ የሚያልፈው ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብን  COVID19 ከተሰኘው የወረርሽኝ መቅሰፍት ለማዳን ያለውን እድል እያጠበባችሁት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

እጃችሁን ስትታጠቡ ፎቶ ተነስታችሁ ማሕበራዊ ሚዲያ ላይ መለጠፉ ምሳሌያዊ በመሆኑ መልካም ቢሆንም በቂ ግን ሊሆን አይችልም። የምታካሂዷቸው ህዝባዊ ስብሰባዎች ለቫይረሱ መሰፋፋት ዋና መንገዶች ናቸው። ነገር ግን ተቀራርቦ ትንፋሽ በመለዋወጥ የሚዛመትን ተስቦ እጅ በመታጠብ ብቻ መግታት አይቻልም። በዚያ ላይ ውሀ እንደልቡ አግኝቶ ቶሎ ቶሎ እጁን በሳሙና መታጠብ የማይችለውንም ህዝብ ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

በአሁኑ ወቅት መላው ዓለም የሰውን ዘር COVID19 ከተሰኘው ወረርሽኝ መቅሰፍት ለመታደግ ማሕበራዊ ርቀት (social distancing) አስፈላጊ መሆኑን አምኖ ስብሰባዎችን በአገደበት ወቅት በአገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ብዙ ሕዝብ የሚከማችባቸው ስብሰባዎች የማካሄድ እሽቅድምድም ይስተዋላል።

ቤተ እምነትን በተመለከተ፣ ጠባቂያችንና አዳኛችን አምላካችን እንደሆነ ስለምናምን ፀሎቱና ምህላው አስፈላጊ ነው። በምእራቡ ዓለም እንደሚታየው የቤተክርስቲያን አባቶች ምእመናቸው አንድ ላይ ተሰብስቦ ለእልቂት እንዳይጋልጥባቸው የቤተክርስቲያን በር ዘግተዋል፤ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን በርቀት የድምፅና ቪዲዮ መገናኛ የቴክኖሎጂ አውታሮች እየሰጡ ነው። ስለሆነም በኢትዮጵያ ያሉት የሃይማኖት አባቶችም በዚህ አስከፊ ወቅት የአገልጋዮችና የምዕመናኑን ደህንነት ለመጠበቅ በሌሎች አገሮች ያሉ አባቶች እንዳደረጉት ወይም ሌላ የተሻለ የሀገራችንን የአኗኗር ዘይቤ ያጋናዘበ አማራጭ ካለ ህዝብ በመጠጋጋትና በመተፋፈግ ለበሽታና ለእልቂት እንዳይጋለጥ ሆኖ እንዲፀልይ መመሪያ መስጠት ይጠበቅባችኋል። እንዲሁም የሀይማኖት አባቶች የሀይማኖቱ ተከታዮች ስለተላላፊው በሽታ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና በምን መንገድ መከላከል እንዳለባቸው ጭምር በእውቀት ማስታጠቅ ከእናንተ ይጠበቃል።

# ሀገሪቱ ላይ ላንዣበበው የወረረሽኝ በሽታ አስጊ አደጋ ተገቢና እውነተኛ እርምጃ

# በመውሰድ ህዝባችንን እንታደገው!ሁሉም በድጋሚ እንዲያውቀው!

በዚህ አስጨናቂ ወቅት ህዝቡን ማስተባበር የምትችሉ የተለያዩ ተቋማት መሪዎች፤ በተለይም የህዝብን ደህንነት መ ጠበቅ ዋና ሀላፊነት ያለባችሁ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለስልጣናት ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥና ወደአጠቃላይ መፍ ትሄ የሚያደርስ እንቅስቃሴ ባፋጣኝ በማድረግ ሕዝቡን ልትታደጉት ይገባል። በመሆኑም የሚከተሉት አስቸኳይ እር ምጃዎች እንዲወሰዱ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት አበክሮ ይጠይቃል።

- *መንግሥት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጆ ማንኛቸውንም ከ10 ሰዉ በላይ የሚገኝባቸውን ስብሰባዎች በሕግ እንዲያግድና የአገሪቱን ሙሉ አቅም በቅድሚያ ወረርሽኙን ለመከላከል እንዲያውል፤*
- *መንግስትና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ችግሩ ባለባቸው ሀገሮች የሚያደርገውን በረራ እንዲያቆምና ሌሎች አየ ር መንገዶችም ወደ ኢትዮጵያ በሚያደርጉት በረራ ላይ ተገቢው ማጣራት እየተደረገ እንዲታገዱ፤*
- *የሀይማኖት፣ የሲቪክ፣ የፖለቲካና የተለያዩ ተቋም መሪዎች መንግስት ያለበትን ሀላፊነት እንዲወጣ ግፊት እንድታደርጉና ከዚያም ባለፈ በራሳችሁ አቅምና በቅንጅት ወገናችንን ከዚህ አስፈሪ ወረርሽኝ  ለመታደግ የድርሻችሁን ትወጡ ዘንድ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት አበክሮ ይማፀናል።*

ማንኛውም ህዝብን ለማገልገል የተቋቋመ ተቋም በዚህ ወሳኝ ወቅት ህዝብን ከእልቂት የመታደግ ግዴታ አለበትና ህዝብን አክብሮ ከምንም ጉዳይ በላይ የህዝብን ደህንነት የመጠበቅ ሀላፊነትና ግዴታ እንዳለበት መዘንጋት የለበትም። ይህ ባይደረግና በቸልተኝነትና በግዴለሽነት የምንፈራው የህዝብ እልቂት ቢፈጠር፣ በትውልድና በታሪክ ፊት ተወቃሽ መሆን በቻ ሳይሆን በህግም ጭምር ተጠያቂነት እንደሚኖር ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት በትህትና ያስገነዝባል። ወቅቱ እኔ ነኝ ያሉ ጠንካራ አገሮችን ያርገደገደ፤ የብዙ ሺ ህዝብ ነፍስ የቀጠፈና በሽታው እንደልቡ ያለማንም ተቆጣጣሪ በአለም የሚናፈስበት ወቅት ስለሆነ የኢትዮጵያውያንን ሕይወት ማዳን ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር  እንደሆነ  እሙን ነው።  ስለዚህ መንግሥት፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች፣የሲቪክ ማህበራትና አክቲቪስቶች ተናባችሁና ተመካክራችሁ በመስራትም ጭምር ህዝቡን ከጥፋት አደጋ ትታደጉት ዘንድ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት በድጋሚ አበክሮ ይማፀናል።

የኢትዮጵያውያንን ሕይወት ማዳን ከምንም ነገር ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው!!

አንድ ዐማራ ለሁሉም ዐማራ፤ ሁሉም ዐማራ ለአድ  ዐማራ!!